# ታሪኩን ይተርኩ

## ጠቃሚ ምክሩን ይማሩ

1. **አንድ ሰው-ፈለገ/ች፡** ስለ ዋናው ገፀ-ባህሪ በማውራት ጀምሩ። በታሪኩ ውስጥ ዋነኛው ሰው (ወይም እንስሳ!) ማን ነበረ? ከአንድ በላይ ሊሆን ይችላል። ይሄ ሰው ምን ነበር የፈለገው?

2. **ግን፡** ቀጥሎም ዋነኛው ገፀ-ባህሪ የፈለገውን ከማግኘት ያገደው ሰው ወይም ነገር ምን እንደሆነ ተነጋገሩ። ይሄም *ችግር* ወይም *ግጭት* በመባል ይታወቃል።

3. **ስለዚህ-ቀጥሎ፡** በመጨረሻም ችግሩ እንዴት እንደተፈታ ተነጋገሩ። ዋነኛው ገፀ-ባህሪ ምን ሆነ/ች? ሁኔታው ተቀየረ? ችግሩን ለመፍታት ያደረጉት ነገር አለ?

### ይሄ ጠቃሚ ምክር ለምን አስፈለገ?

ልጅዎ እጁን/እጇን በመጠቀም ታሪኩን እንዲከልሱ እርዷቸው? ልጅዎ ምስሎችን እያየ/ች ወይም ገፃቹን እያገላበጠ/ች ማብራሪያዎችን ቢ(ብት)ፈልግ ችግር የለውም! ስለታሪኩ ማውራት ልጅዎ ታሪኩን እንዲ(ድት)ረዳው እና እያንዳንዱ ክፍል እንዴት እንደሚገናኝ ለማወቅ ይረዳል። በተጨማሪም—የወደዳችሁትን ታሪክ ማካፈል ደስ ይላል!

## ልጅዎን ይጠይቁ

*በሁሉም እድሜ ክልል፡*

- [አንድ ሰው] ዋናው ገፀ-ባህሪ ማን ነው?
- [ፈለገ/ች] ዋነኛው ገፀ-ባህሪ ምን ነበር የፈለገው?
- [ግን] ምን ተፈጠረ? ገፀ-ባህሪው የገጠመው ችግር ምን ነበር? የፈለጉትን ማግኘት ያልቻሉት ለምንድን ነው?
- [ስለዚህ] ቀጥሎ ምን ተፈጠረ? የገፀ-ባህሪው ችግር እንዴት ተፈታ?
- [ቀጥሎ] ታሪኩ እንዴት ሆኖ አለቀ?

*የእነዚህ አይነት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ልጅዎ ከመፅሀፉ እንዲፈልግ አድርጉ፡*

- እንዴት አወቅህ/ሽ?
- ይሄንን እንድታውቅ/ቂ የረዱህን/ሽን ቃላት ወይም ሀረጎች አሳዩኝ።
- ይሄንን የትኛው ገፅ ላይ ነው የተማርከው/ሽው?

## አዝናኝ ልምም

ታሪኩን በንግግር ከመግለፅ ይልቅ በስዕሎች ግለፁ። እያንዳንድን ማስጀመሪያዎች በወረቀት ላይ ፃፍ/ፊ (አንድ ሰው፣ ፈለገ/ች፣ ግን፣ ስለዚህ፣ ቀጥሎ)። ቀጥሎም ልጅዎ ከቃሉ ስር ስዕል እንዲስል ጋብዙት/ዟት።

ለምሳሌ, “የሆነ ሰው” ለሚለው ልጅዎ የዋና ገፀ-ባህሪውን ስዕል ይሳል/ትሳል። “ፈለገ/ች” ለሚለው ልጅዎ ገፀ-ባህሪው የፈለገውን ነገር ወይም ያጋጠመውን ችግር ይፅፋሉ።